# የሴት ብልት ጉንደላ

የሴት ብልት ጉንደላ በስዊድን ሕግ የተከለከለ ነው (1982:316)።

ሕጉ እንደሚከተለው ነው። —

1 §
የሴትነትን ብልት የውጪ ክፍል ለመቁረጥ ወይም ሌላ ዷሪ ለውጥ እንዲደርስበት ለማድረግ የታቀደ ድርጊት፣ ለድርጊቱ ፈቃደኛነት የተሰጠ ቢሆንም ባይሆንም፣ መፈጸም የለበትም (ሕግ 1998:407)።

2 §
አንቀጽ አንድን የሚጥስ አራት ዓመት ሊደርስ በሚችል እስራት ይቀጣል። ወንጀሉ ለሕይወት አስጊነትን ወይም ጽኑ ህመምን ካስከተለ ወይም በሌላ አኳኋን ከፍተኛ ግድ የለሽነትን ካመለከተ በከባድነት ይታያል። የከባድ ወንጀል ቅጣት አነስተኛው የሁለት ዓመት ከፍተኛው የአሥር ዓመት እስራት ነው። ሙከራ፣ ዝግጅትና ዱለታ እንዲሁም ወንጀልን አለማስታወቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ምዕራፍ 23 መሠረት ያስቀጣል (ሕግ 1998:407)።

3 §
የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ወይም 3 ተፈጻሚነት ባይኖረውም ከላይ የተጠቀሰው ሕግ ወንጀል ያደረገውን ድርጊት የፈጸመ ሰው በስዊድን ፍርድ ቤት ይቀጣል።

LAG MED FÖRBUD MOT KÖNSSTYMPNING AV KVINNOR. SFS NR: 1982:316.
DEPARTEMENT/MYNDIGHET: SOCIALDEPARTEMENTET.
UTFÄRDAD: 1982-05-27. ÄNDRAD: T.O.M. SFS 1999:267. ÄNDRINGSREGISTER: SFSR
KÄLLA: REGERINGSKANSLIET/LAGRUMMET - AMHARISK ÖVERSÄTTNING